## ሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ የአካባቢ ሁኔታ ድጎማዎች ፕሮግራምን ጀምሯል

በአየር ማረፊያ አቅራቢያ ባሉ ማህበረሰቦች ያሉ የአካባቢ ሁኔታ ፕሮጀክቶች የሚደጎሙት እስከ $20,000 በሚደርስ የአቻ ድጎማ ነው

ሲያትል – በአየር ማረፊያ አቅራቢያ ባሉ ማህበረሰቦች ያለውን አካባቢ ሁኔታ ለማሻሻል ማህበረሰብ መር ቡድኖች በአሁኑ ሰአት ለፖርት ኦፍ ሲያትል ፈንድ ማመልከት ይችላሉ። አዲሱ የሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ አካባቢ ሁኔታ ፕሮግራም የሚደግፋቸው ክንውኖች እንደ የህዝብ ቦታ ማሻሻያዎች፣ መሣሪያዎች ወይም ዕደጥበብ ሥራዎች መትከያዎች፣ ወይም የሰፈር ፕሮጀክቶች ወይም የአካባቢ ማሻሻያ ፕሮጀክቶችን በቡሪዬን፣ ደ ሞይንስ፣ ፌዴራል ወይ፣ ኖርማንዲ ፓርክ፣ ሲታክ እና ተክዊላ ውስጥ ናቸው። ማመልከቻዎች መላክ ያለባቸው ከዲሴምበር 4, 2020 ሳያልፍ ነው። የሚሰጡ ድጎማዎች እስከ $20,000 ይሆናሉ።

የኤስኬሲኤፍ የአካባቢ ሁኔታ ድጎማዎች ፕሮግራም የ [ሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ] አዲስ ዙር ነው። የፈንዱ የመጀመሪያው ዙር፣ በኢኮኖሚ ማገገም ላይ ያተኮረ ሲሆን፣ የተጀመረውም በኦገስት 2020 ነው። የኤስኬሲኤፍ የአካባቢ ሁኔታ ድጎማዎች ፕሮግራም ውጤታማ ፕሮግራም የሆነውን [አየር ማረፊያ ማህበረሰብ ኢኮሎጂ (ኤሲኢ) ፕሮግራም] የሲያትል ታኮማ አለም አቀፍ አየር ማረፊያ (ኤስሲኤ) ዙሪያ ላሉ ተጨማሪ ማህበረሰቦች ያስፋፋል። በሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ያሉ ማህበረሰቦች ያልተመጣጠነ የአካባቢ ሁኔታ ጉዳቶች ሲደርስባቸው ይህም ለረጅም ጊዜ በነበረው ኢፍትሓዊ የመሬት አጠቃቀም ተግባራት እና የኢኮኖሚ መፈናቀል ሲሆን ይህም የተነጠሉ ማህበረሰቦችን የበለጠ ወደ ደቡብ አርቆዋቸዋል። በተጨማሪም በኮቪድ-19 የጤና እና የኢኮኖሚያዊ ጫናዎች በዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ህዝቦች እና በባለቀለም ማህበረሰቦች ላይ የባሰ በመሆኑ የተነሳ፣ በሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ውስጥ ከየትኛውም ጊዜ የጠነከረ የኢንቨስትመንት ፍላጎት ስላለ፣ ነዋሪዎች ከተቀሩት የካውንቲ ቦታዎች ሲነጻጸር ነዋሪዎች ለፓርኮች እና አረንጓዴ ስፍራዎች ያላቸው ተደራሽነት ያነሰ ነው።

ፓርቱ ቃል የገባው $10 ሚሊዮን ዶላሮችን በ አሁን እና 2023 መሃከል ለሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ ለመስጠት ነው። ለኤስኬሲኤፍ የአካባቢ ሁኔታ ድጎማዎች ፕሮግራም፣ $435,000 የድጎማ ፈንድ በ 2020 ውስጥ ይገኛል። ፕሮጀክቶች መካሄድ ያለባቸው በህዝባዊ ንብረቶች ሲሆን ማሳየት ያለባቸውም የ 3:1 አቻ ሲሆን፣ ይህም ማለት ለያንዳንዱ በፖርቱ ለተሰጠው ዶላር፣ ሶስት ዶላሮች ከድጎማው ተቀባይ ወይም ከፕሮጀክቱ አጋሮች መገኘት አለበት። ፓርቱ ይህንን አቻ ለማድረግ የሚያቀርባቸው በተለያዩ ዘዴዎች ሲሆን እነዚህም የበጎ ፈቃድ ጊዜ፣ የህዝባዊ ኩነቶች ተሳታፊዎች፣ የግንኙነት ሰኣታት፣ የተተከሉ ዛፎች የዘላለም የአካባቢ ዋጋ ተመን፣ የካርቦን ልቀት ቅነሳዎች፣ የእቃ (በጥሬ ገንዘብ ያልሆኑ) አስተዋጾዎች፣ የፕሮጀክት አጋሮች አስተዋጾዎች፣ እና ጥሬ ገንዘብን ይጨምራል።

“የአካባቢ ሁኔታ ተንከባካቢነት እና የማህበረሰብ ኢንቨስትመንት የኮቪድ   ምላሽ እና ማገገሚያ ስትራቴጂያችን ልብ ውስጥ ያሉ (ዋናዉ አካል) ናቸው፣” ብለዋል ኮሚሽነር Stephanie Bowman. “የሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ማህበረሰቦች በአካባቢ ሁኔታ ፍትሕ የተጫናቸው እና በአየር መንገድ አካባቢ የሚገኙ ማህበረሰብቦች ያሉ ፍትሃዊነት ላይ የተመሰረቱ ኢንቨስትመንቶችን ነው።”

የኤስኬሲኤፍ የአካባቢ ሁኔታ ድጎማዎች ፕሮግራም የኤሲኢ ፈንድ ስራ ሲያስቀጥል፣ ከአየር መንገድ ስራዎች የተነሳ የበለጠ ጫና ያለባቸው የእቅራቢያው ማህበረስቦች የበለጠ ጥቅማ ጥቅሞችን ማግኘት እንዳለባቸው ይረዳል። በ 2016 ከተጀመረ ወዲህ፣ የኤሲኢ ፈንድ ያቀረበው ለ 42 የማህበረሰብ ቡድኖች ከ $360,000 በላይ ትናንሽ የአቻ ድጎማዎች በማህበረሰባቸው ውስጥ ላሉ ለአካባቢ ሁኔታ ማሻሻያ ፕሮጀክቶች ነው። ያለፉት የኤሲኢ ሽልማቶች የደገፉት ፕሮጀክቶች የዋሉት ነባር ተፈጥሮን ለማደስ፣ ወጣቶችን ስለ አካባቢ ሁኔታ እና ዘላቂነት ጉዳዮች ለማስተማር፣ እና ብክለትን ለመከላከል አረንጓዴ የጎርፍ ውሃ መሰረተ ልማቶችን ለመገንባት እና ለማሻሻል ነው። ከዚህ በፊት ስለተደጎሙ የኤሲኢ ፕሮጀክቶች ሙሉ ዝርዝር [እዚህ] ይገኛሉ።

### *ሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ*

የፖርት ኦፍ ሲያትል የ [ሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ፈንድ] ን በ 2019 ያቋቋመው ፍትሓዊነትን ያማከለ አጋርነቶችን ለማጎልበት እና ድጋፎችን በታሪክ በዝቅተኛ ደረጃ ለተገለገሉ የአየር ማረፊያ አቅራቢያ ማህበረሰቦችን ለማገዝ እና ድጋፍ ለማቅረብ፣ የድምጽ ብክለትን ለመቋቋም፣ የአካባቢ ሁኔታ እና ዘላቂነትን ለማረጋገጥ ነው። በኮቪድ-19 ከባድ ቀውስ ምላሽ ለመስጠት ሲባል፣ የፓርቱ ኮሚሽን የኢኮኖሚያዊ እድገትን እንደተጨማሪ ትኩረት በማድረግ ድጎማ ለማድረግ ወስኖዋል። የፈንዱ የመጀመሪያ የድጎማ ዙር፣ በአሁኑ ሰኣት እየተካሄደ ያለው፣ ያተኮረው ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጫና ለማገገም ባሉትን የአካባቢው ማሻሻያዎች ላይ ነው። ይህም የሚጨምረው የአካባቢ ሁኔታ ማሻሻያዎችን ሲሆን፣ ይህም የአረንጓዴ ስፍራ መኖር ከመቼውም ጊዜ የበለጠ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ነው።

“በነዚህ የወረርሽኙ ፈታኝ ጊዜያት፣ ማህበረሰቦቻችን የበለጠ ጊዜያቸውን በውጪ በመማር፣ የጓሮ ሥራ፣ እና በአካባቢው ፓርክ ላይ የእግር ጉዞ በማድረግ እያሳለፉ ነው። በሳውዝ ኪንግ ካውንቲ ያሉ የአካባቢ ሁኔታ ፕሮጀክቶችን በመደገፍ፣ ባብዛኛው ጤናማ ምግቦችን ለማሳደግ አቅም የሌላቸውን ማህበረሰቦች ስናጠነክር፣ እንዲሁም አዳዲስ ግንኙነቶችን እንዲያገኙና ለወደፊት ቅጥር አዳዲስ ክህሎቶችን እንዲማሩ እድል እንሰጣለን፣” ብላለች ቪኪ ናቫሮ፣ የፌዴራል ወይ ነዋሪ።

ማመልከቻዎን ከ ዲሴምበር 4, 2020 12:00 ፒኤም በፊት ይላኩ።

ተጨማሪ ዝርዝሮች እና የማመልከቻ መረጃዎች በዚህ ይገኛሉ https://www.portseattle.org/programs/south-king-county-fund-environmental-grants-program.